# በኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ሒደት የሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶች የተሳትፎ መመሪያ

**ግንቦት 2015**


አዘጋጆች

**ሶሊያና ሽመልስ**

**ቃልኪዳን ኢሳያስ (ዶ/ር)**

## ማውጫ


ዐብይ ጭብጥ.........2

1. መግቢያ.........3

   1.1. የአገራዊ ምክክር ትርጓሜ.........3

   1.2. አገራዊ ምክክሮች የሚፈጠሩባቸው አጋጣሚዎች.........3

   1.3. የአገራዊ ምክክር ማዕቀፍ እና ምዕራፎች.........4

      1.3.1. የዝግጅት ምዕራፍ.........4

      1.3.2. የሒደት ምዕራፍ.........4

      1.3.3. የትግበራ ምዕራፍ.........4

   1.4. የአገራዊ ምክክሮች ወሳኝ አካላት.........5

   1.5. አገራዊ ምክክር በኢትዮጵያ.........5

2. የመመሪያው ዓላማ እና ወሰን.........6

3. የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች እና የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች በአገራዊ ምክክር ሒደት ውስጥ የሚጫወቱት ሚና 6

   3.1. ግንዛቤ ማስጨበጥ.........6

   3.2. ክትትል እና ትዝብት.........6

   3.3. ተሟጋችነት/አድቮኬሲ.........7

   3.4. ተሳትፎ.........7

4. የተሳትፎ መርሆዎች.........7

   4.1. የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች በአገራዊ ምክክር ተሳትፏቸው ላይ ሊኖሯቸው የሚችሉ ዓላማዎች፣ ተግባራት እና ስልቶች 9

   4.2. በአገራዊ ምክክር ሒደት ከሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶች ጋር የሚሠሩ ባለድርሻ አካላት.........11

   4.3. የሰብአዊ መብቶች ድርጅቶች ሊያጋጥሟቸው የሚችሉ ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ የሚወሰዱ እርምጃዎች.........12

   4.4. የሥነ ምግባር ደንብ.........13

ማጣቀሻ ሰነዶች.........14

አባሪ 1፤ የኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ኮሚሽን አባላት.........15

አባሪ 2፤ የተሳታፊ ድርጅቶች ዝርዝር.........16

   ሀ) በምክክር ዐውደ ጥናት ወቅት ተሳታፊ ድርጅቶች.........16

   ለ) በማመሳከሪያ ዐውደ ጥናት ወቅት ተሳታፊ ድርጅቶች.........17

# ዐብይ ጭብጥ

አገራዊ ምክክሮች ፖለቲካዊ ቀውሶችን ለመፍታት እንዲሁም ዘላቂ ሰላም ለማምጣት እና ሰላማዊ የፖለቲካ ሽግግር ለማድረግ መሠረትን ለመጣል ዋነኛ ዘዴ ሆነው ያገለግላሉ። በኢትዮጵያ ከሚስተዋሉት ሥር የሰደደ እንዲሁም ወቅታዊ የፖለቲካ እና ማኅበራዊ ቅራኔዎች አንፃር፤ አገራዊ ምክክር ለግጭት መሠረት ከሆኑ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ጠቃሚ ንግግሮችን ለማድረግ እና ለእነዚህ ጉዳዮች ሁሉን ያካተተ መፍትሔ እንደሚሰጥ ይታመናል። አገራዊ ምክክር በአብዛኛው መፍትሔ ያጡ የፖለቲካ ውጥረቶችን ለማስወገድ እንዲሁም ቀውስ የሚያስከትሉ ግጭቶችን ለማስቆም እና ሰላማዊ የፖለቲካዊ ሽግግሮችን ለማምጣት ይረዳል።

በአገራዊ ምክክር ሒደትና ውጤት ላይ በመሳተፍ የበኩላቸውን አስተዋፅዖ ማድረግ የሚጠበቅባቸው የተለያዩ ባለድርሻ አካላት አሉ። ከነዚህም መካከል የሲቪክ ማኅበረሰብ ድርጅቶች (ሲማድ) በተለይም ደግሞ የሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶች ትልቁን ድርሻ ይወስዳሉ።

ይህ መመሪያ የሰብአዊ መብቶች ድርጅቶች (ሰማድ) እና የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች (ሰመተ) በአገራዊ ምክክር ሒደት ውስጥ የሚሳተፉባቸውን ሁኔታዎች ለመወሰን የሚጠቅሙ ዘዴዎችን ለመጠቆም ያለመ ነው። ይህም በኢትዮጵያ በሚደረገው የአገራዊ ምክክር የዝግጅት፣ የሒደት እና የትግበራ ወቅት ላይ መከናወን ያለባቸውን ተግባራት ያካተተ ነው።

ይህ መመሪያ የተዘጋጀው ከሚመለከታቸው የሰመድ ተወካዮች ጋር የውይይት መድረኮችን በማከናወን የተገኙ ግብዓቶችን በማሰባሰብ ነው።

# 1. መግቢያ

## 1.1. የአገራዊ ምክክር ትርጓሜ

አገራዊ ምክክር ማለት *"በፖለቲካዊ ቀውስ ወቅት፣ ወይም ከጦርነት በኋላ በሚከሰቱ ሁኔታዎች ወይም በፖለቲካዊ ሽግግሮች ወቅት፣ በተለያዩ የአገር ውስጥ ባለድርሻ አካላት መካከል መግባባት ለመፍጠር በአገር ዐቀፍ ደረጃ የሚካሔድ ፖለቲካዊ ሒደት"* ነው።[1]

አገራዊ ምክክር ለግጭት አፈታት እና የፖለቲካ ለውጦችን ለመምራት ከጊዜ ወደ ጊዜ ተመራጭ እየሆነ የመጣ መሣሪያ ነው። ከተለመደው የልሒቃኖች ውሳኔ ሰጪነት ሚና እና የምርጫ ዑደቶች ባሻገር የአንድን አገር አካሔድ በተመለከተ ሰፋ ያለ ኅብረተሰብ የሚያሳትፍ ውይይት እና ክርክር እንዲኖር ያስችላል። ግጭት ውስጥ ባሉ የፖለቲካ ኃይሎች መካከል የሚስተዋሉ ዋና ዋና የፖለቲካ ልዩነቶችን ለመፍታት እና የተዳፈኑ ግጭቶችንና ውጥረቶችን ለማስወገድ እንዲሁም መግባባትን ለመፍጠር ከሚጠቅሙ መሣሪያዎች ውስጥ አንዱ ነው። አገራዊ ምክክር የፖለቲካ ቀውሶችን ለመፍታት እንዲሁም ፖለቲካዊ ሽግግር እና ዘላቂ ሰላም ለማምጣት መንገዶችን በማመቻቸት ረገድ ሁነኛ መሣሪያ በመሆን እያገለገለ ነው።[2]

አገራዊ ምክክሮች በዋነኛነት ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍሎች በማሳተፍ ሰፊ የምክክር መድረኮችን ያከናውናሉ። አካሔዱም አዲስ ማኅበራዊ ውል ለመመሥረት እንዲሁም ተጨማሪ አገራዊ ዓላማዎች ለመፍጠር የሚያስችሉ ሰፊ ይዘት ያላቸውን ምክክሮችን ያካትታሉ።

አገራዊ ምክክር የሚካሔድበት የፖለቲካ ዐውድ ሒደቱ የሚሳካበት ወይም የሚከሽፍበት ዕድል ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል። ከነዚህም ውስጥ ዋነኞቹ፣ የፖለቲካ ቁርጠኝነት፣ ሌሎች ከሽግግር ሒደቶች ጋር የተገናኙ ሁኔታዎች፣ በፓርቲዎች መካከል ያለ የጋራ ሥምምነት፣ ሕዝባዊ ቅቡልነት፣ ካለፈው ልምድ የተቀሰመ ትምህርት፣ የውጭ ባለድርሻዎች ሚና እና የአገር ባለቤትነት ጉዳዮዮች ይገኙበታል።[3]

## 1.2. አገራዊ ምክክሮች የሚፈጠሩባቸው አጋጣሚዎች

ብዙ አገራዊ ምክክሮች የሚፈጠሩት ሕዝባዊ ነውጦች፣ ጦርነት ወይም የትጥቅ ትግሎች እና/ወይም ልኂቃኖች በብቸኝነት አመፅን በድርድር የሚፈቱበት የፖለቲካ አውድ ውስጥ ነው። አገራዊ ምክክሮች በተለያዩ አካላት ተነሳሽነት ሊጀመር ይችላል። ተቃዋሚ ፓርቲዎች፣ መንግሥት እና ሲቪክ ማኅበራት በተለያዩ ምክንያት አገራዊ ምክክሮች እንዲጀምሩ ሲሟገቱ ይታያል። በአጠቃላይ አገራዊ ምክክሮች እያሻቀቡ ለሚሔዱ አገራዊ ውጥረቶች ምላሽ ለመስጠት የሚደረጉ ሲሆን፣ ብዙውን ጊዜ በፖለቲካ ቀውስ እና አጣብቂኝ ውስጥ የሚከናወኑ ናቸው። ይህም በተለይ መሠረታዊ አገራዊ ጉዳዮች ላይ ጥያቄ ሲነሳ ወይም የገዥው መንግሥት ኅልውና ጥያቄ ውስጥ ሲገባ የሚስተዋል ጉዳይ ነው።[4]

---

[1] Blunck et al., 2017

[2] Paffenholz et al., 2017
[3] Haider, 2019
[4] Paffenholz et al., 2017

## 1.3. የአገራዊ ምክክር ማዕቀፍ እና ምዕራፎች

### 1.3.1. የዝግጅት ምዕራፍ

አገራዊ ምክክሮች በሦስት ተከታታይ ደረጃዎች ያልፋሉ፡- ዝግጅት፣ ሒደት እና ትግበራ። የአገራዊ ምክክር የዝግጅት ምዕራፍ በጣም ወሳኝ እና ቀጣዮቹን ምዕራፎች ለማተካከል ወሳኝ ክፍል ነው። ስለዚህም በቂ ጊዜ በተለይም በአንዳንድ ሁኔታዎች የሒደቱ ምዕራፍ ከሚወስደው ጊዜ የበለጠ ረዘም ያለ ጊዜ መመደብ ያስፈልጋል። በዚህ ምዕራፍ ቢያንስ ምክክሩ ሊከተላቸው የሚገቡ ዋና ዋና የምዘና መሥፈርቶች ላይ ሥምምነት ላይ መደረስ አለበት። ከተለመዱት የምዘና መሥፈርቶች ውስጥ የአገራዊ ምክክሩ ሥልጣን፣ የምክክር አጀንዳዎች፣ የተሳታፊዎችን ምርጫ፣ አመቻች እና አባላት አመራረጥ፣ የውሳኔ አሰጣጥ አካሒዶች፣ ወዘተ. ይካትታሉ።

የዝግጅት ምዕራፉ ሰላማዊ እና ስኬታማ አገራዊ ምክክሮች እንዲካሔዱ መሠረት ለመጣል የሚያስፈልጉ ተቋማትን እና አሠራሮችን በግልጽ ማስቀመጥ ይኖርበታል። በተጨማሪም የተለያዩ ችግሮች እና ተግዳሮቶች ሊፈጠሩ እንደሚችሉ የሚጠበቅበት እና በተከሰቱ ሰዓትም ለመፍታት የሚያስችሉ አሠራሮች ቀደም ብለው የሚዘረጉበት ምዕራፍ ነው።

በዚህ የዝግጅት ምዕራፍ ውስጥ በምክክሩ ዋና ዋና ዓላማዎች ላይ የጋራ መግባባት ላይ መድረስ ያስፈልጋል። ከዓላማዎቹ ውስጥ ነውጥን ማቆም፣ የመንግሥት እና የኅብረተሰብ ግንኙነቶችን እንዲሁም የፖለቲካ ስርዓቱን እንደገና መልሶ መገንባት እና የመሳሰሉት የሚካተቱ ይሆናል። ግልጽ ዓላማዎች መቀመጣቸው የምክክሩን መዋቅር፣ ሒደቱን እና ውጤቱን ይወስናል። የእምነት ግንባታ እና ቴክኒካዊ አቅም መገንባት በዝግጅት ምዕራፍ ውስጥ ቁልፍ ጉዳዮች ናቸው።

### 1.3.2. የሒደት ምዕራፍ

ቁልፍ የሚባሉት የምዘና መሥፈርቶች ከተቀመጡ በኋላ የአገራዊ ምክክር ሒደት ምዕራፍ ይጀምራል። ይህ ምዕራፍ ለሁሉም በግልጽ የሚታይ የአገራዊ ምክክሩ ዋነኛ አካል ነው። ሕጋዊ የሆነ የአገራዊ ምክክር ምዕራፍ ሲሆን፥ ከትግበራ ጋር የተያያዙ ዋና ዋና ጉዳዮችን ይሸፍናል። ዋና ዋና ከሚባሉ ከትግበራ ጋር ከተያያዙ ጉዳዮች ውስጥ አጀንዳ መቅረፅ፣ ምክክር አመቻች የሚሆን አካል መምረጥ፣ መተዳሪያ መርሖዎችን ማውጣት፣ የውሳኔ አሰጣጥ ዘዴዎችን ማዘጋጀት፣ ተሳታፊዎችን መምረጥ፣ ሕዝባዊ ውይይቶችን እና ተደራሽነትን ማረጋገጥ፣ ውጤታማ የድጋፍ መዋቅሮችን ማቋቋም እና ስለ ጊዜ እና ቅደም ተከተል ማቀድ እና የመሳሰሉ ይገኙበታል።[5]

### 1.3.3. የትግበራ ምዕራፍ

የትግበራው ምዕራፍ በምክክሩ ወቅት የተላለፉ ውሳኔዎችን እና ምክረ ሐሳቦችን ለማስፈፀም ያለመ ነው። በአገራዊ ምክክር የተገኙ ምክረ ኀሳቦች እና ውሳኔዎች የሚተገበሩበት ጊዜ ማለት ለተሳታፊ አካላት እና አስተባባሪዎች የመጨረሻው ተግዳሮት የሚያጋጥምበት ወቅት ነው። ስለሆነም ምክክሩ በሚካሔድበት ወቅት እና ከተካሔደ በኋላ ስለሚያጋጥሙ ሁኔታዎች በጥንቃቄ መታቀድ አለበት። እንደ አገራዊ ምክክሩ ዓላማ እና የተሰጠው ሥልጣን፣ ትግበራውን የተመለከተ ዕቅድ የሚከናወነው በሒደት ምዕራፍ ወይም ቀደም ብሎ በዝግጅት ምዕራፍ ወቅት ሊሆን ይገባል።[6]

---

[5] (Blunck et al, 2017).
[6] (Blunck et al., 2017).

## 1.4. የአገራዊ ምክክሮች ወሳኝ አካላት

አገራዊ ምክክሮች በጣም የተወሳሰቡ እና በሁኔታዎች ዐውድ ላይ የተመሠረቱ ሒደቶች የሚከናወኑባቸው ቢሆንም ሒሂደቱ በሚቀረፅበት ወቅት በጣም አስፈላጊ የሆኑ እና የተለመዱ ቁልፍ ክፍሎች አሏቸው፡፡

1. የአገራዊ ምክክር አስተባባሪ አካል ሥልጣን
2. አጀንዳ መቅረፅ
3. የተሳታፊዎች ምርጫ እና አካታችነት
4. ግልጽ የውሳኔ አሰጣጥ ሒደት

አገራዊ ምክክርን እንዲሳካ ወይም እንዲከሽፍ የሚያደርጉ ሁኔታዎች ምንድን ናቸው?

- የፖለቲካ ቁርጠኝነት
- የልኂቃን ድጋፍ ወይም ተቃውሞ
- ሌሎች የሽግግር ጉዳዮች እና ክንውኖች
- በተሳታፊ አካላት መካከል የሚኖር የጋራ ጉዳይ
- ሕዝባዊ ይሁንታ ወይም ቅሬታ
- ካለፉ ልምዶች የተቀሰሙ ትምህርቶች
- የምክክር እና የውይይት ባሕል
- የውጭ አካላት ሚና እና የአገሬው የሒደቱ ባለቤትነት ጉዳይ
- ውክልና፣ የተሳታፊዎች ብዛት እና የባለድርሻ አካላት ምርጫ
- መተማመንን ለመገንባት የሚወሰዱ እርምጃዎች
- የውሳኔ አሰጣጥ ሒደቶች
- የአመቻቾች እና የአስተባባሪዎች አመራረጥ

## 1.5. አገራዊ ምክክር በኢትዮጵያ

አገራዊ ምክክር በኢትዮጵያ የፖለቲካ መነጋገሪያ ርዕስ መሆን ከጀመረ በርካታ ዐሥርት ዓመታትን አስቆጥሯል፡፡ የኢሕአዴግ መራሹ መንግሥት ሥልጣን ከያዘበት ከ1983 ጀምሮ የፖለቲካ ፓርቲዎች አገራዊ ምክክር መደረግ እንዳለበት ሲወተውቱ ቆይተዋል፡፡ ሐሳቡ ከብዙ የፖለቲካ ባለድርሻ አካላት ቢነሳም መንግሥት በኢትዮጵያ ውስጥ አገራዊ ምክክር አያስፈልግም የሚል አቋም በመያዙ ፀንቶ ቆይቶ ነበር፡፡

በ2010 የጀመረውን የፖለቲካ ስርዓት ለውጥ ሒደት ተከትሎ አገራዊ ምክክር የሚለው ሐሳብ ዳግም የፖለቲካ ተዋስዖው አካል ሆኖ ተመለሰ፡፡ ከአገራዊ ምክክር ጋር ተቀራራቢ የሆኑ ተነሳሽነቶችም ተፈጥረው ነበር፡፡ በ"ዴስቲኒ ኢትዮጵያ" ይዘጋጅ የነበረው በፖለቲካ መሪዎች እና ተፅዕኖ ፈጣሪ ሰዎች መካከል የሚደረግ ውይይት፣ እንዲሁም በፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት የተዘጋጀው "የፖለቲካ ፓርቲ የእርስበርስ ምክክር" ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ሊሆኑን ይችላሉ፡፡ ዴስትኒ ኢትዮጵያ ካካሔዳቸው ውይይቶች የተገኙ ግኝቶችን[7] ይፋ ያደረገ ሲሆን የፖለቲካ ፓርቲዎች የጀመሩት ውይይት የአገር ዐቀፍ ምርጫ ጉዳይ ትኩረት ተነፍጎት ተቋርጧል፡፡ የዴስቲኒ ኢትዮጵያ ተነሳሽነት ከጊዜ በኋላ ተስፋፍቶ እና ተጨማሪ አካላት ተሳትፈውበት ማይንድ ኢትዮጵያ የሚል ሥያሜ በመያዝ ፖለቲካዊ ምክክሮችን ያካሒድ ነበር፡፡ በኋላ ላይም አገራዊ ምክክር ኮሚሽን ለመመሥረት አስተዋፅዖ ካደረጉት ተቋማት አንዱ ነው፡፡

ከእነኚህ የተበታተኑ ጅምሮች መሐል፣ የኢትዮጵያ መንግሥት ከ2013 አገራዊ ምርጫ በኋላ ሁሉን ያካተተ አገራዊ ምክክር ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ እንደሆነ አስታወቀ፡፡ በታኅሣሥ 20 ቀን 2014 የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅን አፅድቋል፡፡ ኮሚሽኑንን የሚያቋቁመው አዋጅ ኮሚሽኑ የሚያስፈልገው "ለአገራዊ መግባባት እና ጠንካራ ቅቡልነት ያለው አገረ መንግሥት ለመገንባት ፅኑ መሠረት መጣል" እንደሆነ ይገልጻል፡፡

የኮሚሽነሮቹን ሥያሜ በተመለከተ፣ ለሕዝብ ይፋ ያልተደረጉ ስድስት መቶ ሰላሳ ሁለት (632) እጩዎችን በመመዝገብ ከነሱ መካከል የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አርባ ሁለት (42) እጩዎችን በመምረጥ፣ በመጨረሻ ዘጠኝ (9) ኮሚሽነሮች ተለይተዋል፡፡ እንዲሁም ከስድስት መቶ ሰላሳ ሁለት (632) እጩዎች ውስጥ አርባ ሁለቱ ውስጥ ያልገቡ ሁለት (2) እጩዎችን በመጨመር በአጠቃላይ ዐሥራ አንድ (11) ኮሚሽነሮች ተሾመዋል፡፡ ኮሚሽኑ ካሉት ዐሥራ አንድ ኮሚሽነሮች ሁለቱ ሴቶች ናቸው (አባሪ 1)፡፡

[7] https://forumfed.org/document/destiny-ethiopia-four-scenarios-of-possible-futures/

በኮሚሽነሮች አመራረጥ ሒደት ግልጽነት ላይ ጥያቄዎች የተነሱ ሲሆን አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች ግልጽነት የጎደለው መሆኑን እና የኮሚሽነሮች አሰያየም ሒደት ላይ መንግሥት ጣልቃ እንደገባ እና ተፅዕኖ እንዳሳደረ በመግለጽ በሒደቱ ላለመሳተፍ መወሰናቸውን አስታውቀዋል።[8] በአንዳንድ ክልሎች፣ አንድ ዓይነት ባይሆኑም፣ በክልል መንግሥታት የሚመሩ እና በክልል ደረጃ ተለይተው የሚንቀሳቀሱ ጅምሮችም አሉ። የሶማሌ ክልል የእውነት እና እርቅ ኮሚሽን እና የትግራይ ክልል የዘር ማጥፋት ወንጀል መሰነድ ጅምሮች እንደ ምሳሌ ሊጠቀሱ ይችላሉ።

# 2. የመመሪያው ዓላማ እና ወሰን

ይህ "በኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ሒደት የሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶች የተሳትፎ መመሪያ" ሰነድ የተዘጋጀው በመብቶች እና የዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል (ካርድ) እና በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች ማዕከል ሲሆን፥ ሲቪል ራይትስ ዲፌንደርስ የፋይናንስ ድጋፍ አድርጎበታል። ለመመሪያው ግብዓት የሆኑት ሐሳቦች የተሰበሰቡት ከሌሎች የሚመለከታቸው የሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶች ጋር ከተደረጉ አሳታፊ ምክክሮች እና ዐውደ ጥናቶች ነው (አባሪ 2)።

የዚህ መመሪያ ዓላማ በመጪዎቹ የኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ሒደቶች ውስጥ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች እና ድርጅቶች ተሳትፎ ምን መምሰል እንዳለበት አቅጣጫ ማስያዝ ነው። የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ትኩረት ሰጥተው ከመንቀሳቀሳቸው አንፃር የሰብአዊ መብት ጉዳዮችን እና አጀንዳዎችን የውይይቱ አካል እንዲሆኑ በማድረግ ረገድ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ይጠበቃል። ስለዚህ ይህ መመሪያ ምንም እንኳን ለሌሎች የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ሊጠቅም የሚችል ቢሆንም፥ በዋነኝነት የተዘጋጀው የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ድርጅቶች በእያንዳንዱ የአገራዊ ምክክር ሒደት ውስጥ ካላቸውን ሚና በተጨማሪም ከአገራዊ ምክክር ሒደቶች በኋላ የሚኖሩ እንቅስቃሴዎች እና ተግባራት ዙሪያ ለሚኖራቸው ተሳትፎ በማመሳከሪያነት እንዲጠቀሙበት ነው።

መመሪያው ከኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ጋር የተያያዙ ተግባራዊ እና ንድፈ ሐሳባዊ ጉዳዮችን ይሸፍናል። የተሳትፎ መንገዶችን ይጠቁማል። የተሳትፎ ዓላማዎችን ይለያል እንዲሁም በየደረጃው በሚኖሩ ተሳትፎዎች ሒደት ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ዘዴዎችን ይጠቁማል። ድርጅቶቹ በዚህ የመመሪያ ሰነድ ላይ በመመሥረት ፕሮጀክቶችን ማስፋፋት፣ መንደፍ እና ሚናቸውን እና ዓላማቸውን በዝርዝር ማስቀመጥ ይችላሉ።

መመሪያው ለሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ድርጅቶች ፕሮጀክቶችን፣ ተግባራትን፣ ዘመቻዎችን እና ሌሎች ከአገራዊ ምክክር ጋር የተያያዙ ዕቅዶች ሲነድፉ ለመነሻነት የሚሆን ሰነድ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል።

# 3. የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች እና የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች በአገራዊ ምክክር ሒደት ውስጥ የሚጫወቱት ሚና

የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች እንደ አገራዊ ምክክር ሒደት ያሉ ትልቅ አገራዊ ሒደቶች ወሳኝ ተዋናዮች ናቸው። ለምሳሌ በቱኒዝያ "ናሽናል ዲያሎግ ኳርቴት" በመባል የሚታወቀው የአራት ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ጥምረት ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ያመራውን አገራዊ ምክክር መርተዋል። እነዚህ አራቱ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች የምክክር መድረኮችን ራሳቸው የማዘጋጀት እና የማስተባበር ድርሻ ነበራቸው። በሌሎች ሁኔታዎች ደግሞ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በእያንዳንዱ ደረጃ ላይ በተለያየ መልኩ በመሳተፍ በሒደቱ ላይ ተፅዕኖ ያሳድራሉ። የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች እና የሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶች ሊኖሯቸው ከሚችሉት የተወሰኑ ሚናዎች መካከል:-

## 3.1. ግንዛቤ ማስጨበጥ

የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ከብዙኃን ጋር የሚያገናኙ ሥራዎችን የሚሠሩ እና ከፖለቲካ ፓርቲ የራቁ ድርጅቶች እንደመሆናቸው አገራዊ ምክክርን በተመለከተ የሚነሱ ሐሳቦችን እና ትርጓሜዎች ግልጽ ማድረግ እንዲሁም በእያንዳንዱ የሒደቱ ደረጃ ላይ ግንዛቤን የማስጨበጥ ሚና ሊወስዱ ይችላሉ። በዚህ ሚናቸው በሒደቱ ላይ ሰፊው የማኅበረሰብ ክፍል የሚኖረውን ንቁ እና ትርጉም ያለው ተሳትፎ ለማሳደግ ከፍተኛ ተፅዕኖ ይኖራቸዋል።

## 3.2. ክትትል እና ትዝብት

የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አጠቃላይ የክትትል እና ትዝብት (monitoring and observatin) ሒደቱን የመመዝገብ እና የሒደቱን ሪፖርት ለሰፊው ሕዝብ እና ለባለድርሻ አካላት ማቅረብ ይችላሉ። የማኅበራቱ የክትትል እና ሒደቱን የመመዝገብ ሥራ አገራዊ ምክክርን በሚመለከት አድቮኬሲ ሥራ ላይ ለመሳተፍ ለሚፈልጉ ቡድኖች እና ድርጅቶች ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው።

[8] https://addisstandard.com/news-newly-formed-caucus-sets-conditions-for-restructuring-reforming-planned-national-dialogue/

## 3.3. ተሟጋችነት/አድቮኬሲ

የሲቪክ ማኅበረሰብ ድርጅቶች ከአገራዊ ምክክር ጋር በተያያዙ የተለያዩ የተሟጋችነት ወይም አድቮኬሲ ሥራዎች ላይ መሳተፍ ይችላሉ። ይህም የሆነ ቡድን እና/ወይም አጀንዳ እንዲካተት መሟገት እንዲሁም የሒደቱን የተለያዩ ደረጃዎች ማጣራትን ይጨምራል። እንዲሁም አገራዊ ምክክሩ በተቀመጠለት ዓላማ መሠረት የተሻለ ውጤት እንዲመጣ በአስተባባሪዎች እና በተሳታፊዎች ላይ ጫና መፍጠር።

## 3.4. ተሳትፎ

የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች እንደ የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ተወካዮች እንደመሆናቸው መጠን ስለዚህ በምክክር መድረኮች እና የተሳታፊዎች ምርጫ ላይ መሳተፍ፣ አጀንዳ ማስቀመጥ እና በመሳሰሉጽ መንገዶች በመሳተፍ ሒደቱን ቅርፅ በማስያዝ መሳተፍ ይችላሉ።

የሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶች እንደ ሌሎች የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ተመሳሳይ ሚና ሊኖራቸው ቢችልም ግን የሰብዓዊ መብቶችን በተመለከተ የሚሠሯቸው ተግባራት በመኖራቸው ምክንያት ከወቅታዊው የኢትዮጵያ ሁኔታ ጋር ተያያዥነት ባላቸው ሒደቶች ውስጥ ከሰብዓዊ መብቶች ጋር በተያያዘ መርሖዎች፣ ዓላማዎች እና ውጤቶች እንዲመዘገቡ የተለየ ሚና ይኖራቸዋል።

# 4. የተሳትፎ መርሆዎች

የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ድርጅቶች ከሚመሩባቸው አጠቃላይ መርሖዎች በተጨማሪ በተለያዩ አገራዊ ምክክር ሐደት ውስጥ በሚሳተፉበት ጊዜ የተለዩ የተሳትፎ መርሖዎች ያስፈልጓቸዋል። እነዚህም የሚከተሉትን ይጨምራሉ፡-

- **ገለልተኝነት፤** አገራዊ ምክክር በጣም አከራካሪ የፖለቲካ ሒደት እንደመሆኑ መጠን የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ድርጅቶች በተቻለ መጠን ከፖለቲካ እና ከፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም ገለልተኝነታቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል።

- **ነጻነት፤** የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ድርጅቶች ከባለድርሻ አካላት፣ ከለጋሽ አካላት እና ሌሎች ፍላጎቶች ካላቸው አካላት ተፅዕኖ ነጻ ሆነው በሒደቱ ላይ ራሳቸውን ችለው መሳተፍ አለባቸው።

- **ግልጽነት እና ተጠያቂነት፤** የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ድርጅቶች በአገራዊ ምክክር ላይ የሚኖራቸው ተሳትፎ ግልጽ ሊሆን ይገባል። እንዲሁም ከምክክር ሒደቱ ጋር በተያያዘ ለሚያከናውኗቸው ተግባራት እና እንቅስቃሴዎች ኃላፊነትን ሊወስዱ ይገባል።

- **የሰብዓዊ መብቶች ተኮር አካሔድ፤** የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ድርጅቶች ተሳትፎ በሰብዓዊ መብቶች ተኮር ተግባራት ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት። ይህም ሰብዓዊ መብቶችን ጉዳይ የምክክር ሒደቱ ማዕከል እንዲሆን ለማስቻል ከሌሎች ፖለቲካዊ እና ማኅበራዊ አጀንዳዎች በተጨማሪ ከሰብዓዊ መብቶች ጋር ተያያዥ የሆኑ ርዕሶችን ወደ መድረክ እንዲመጡ ማድረግ ማለት ነው።

- **አካታችነትን ማበረታታት፤** አካታችነት ከሰብዓዊ መብቶች መሠረታዊ መርሖች አንዱ እንደመሆኑ መጠን በአገራዊ ምክክር ሒደት ላይ የተሠማሩ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ድርጅቶች የተገለሉ ቡድኖች እንዲካተቱ እና ድምፃቸው እንዲሰማ የማድረግ ልዩ ኃላፊነት አለባቸው። እንዲሁም አካታችነትን የተመለከቱ ርዕሶች በተለያዩ የአገራዊ ምክክር ምዕራፎች ውስጥ መካተታቸውን ማረጋገጥ ይችላሉ።

- **ተሳትፎ ላይ ማተኮር፤** የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ድርጅቶች በተወሰነ የሰብዓዊ መብቶች አጀንዳ ላይ ልዩ ትኩረት እንዲሰጡ እና ጉዳዩም የምክክር ሒደቱ አካል መሆኑን ሊያረጋግጡ ይገባል። በርከት ያሉ ወይም የተለያዩ ርዕሰ

ጉዳዮችን ይዘው መቅረባቸው ተሳትፎአቸውን የሚያመጣውን ተፅዕኖ ሊገድብ ይችላል። ብዙ የሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶች የአቅም ውስንነት አለባቸው። ስለሆነም ትርጉም ያለው ተፅዕኖ ለማሳደር በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ብቻ ማተኮር ኀብትን ለመቆጠብ እና በአግባቡ ለመጠቀም ይረዳል።

- **ትብብር፤** የሰብአዊ መብቶች ተሟጋች ድርጅቶች ሌሎች ድርጅቶች ያከናወኗቸውን ተግባራት ድጋሚ በመሥራት የሚመጣ ድካም እና ኪሳራን  በማስወገድ እርስ በርሳቸው ተባብረው/ተናበው በመሥራት ያለውን ውሱን ሀብት በመቆጠብ በሒደቱ ላይ ትርጉም ባለው መልኩ ተፅዕኖ ማሳደር አለባቸው።

## 4.1. የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች በአገራዊ ምክክር ተሳትፏቸው ላይ ሊኖሯቸው የሚችሉ ዓላማዎች፣ ተግባራት እና ስልቶች

የአገራዊ ምክክር ምዕራፎች፣ በየምዕራፉ ያሉ ዓላማዎች፣ ሊከናወኑ ከሚችሉ ተግባራት እና ጠቃሚ ዘዴዎች ጋር በሰንጠረዥ 1 ላይ ተቀምጠዋል። የሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶች ይህንን መሠረታዊ መመሪያ በማስፋት ፕሮጀክቶችን ማዘጋጀት እና/ወይም ተግባራቶችን በሚያወጡበት ወቅት እንደ ማመሳከሪያነት ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

**ሰንጠረዥ 1.** የሰብአዊ መብት ድርጅቶች በአገራዊ ምክክር የሚኖራቸው ተሳትፎ

| የአገራዊ ምክክር ምእራፍ | የሰብአዊ መብት ድርጅቶች ተሳትፎ ዓላማ | በሰብአዊ መብት ድርጅቶች ሊከናወኑ የሚችሉ ተግባራት | ጠቃሚ ዘዴዎች | ቁልፍ ውጤቶች |
|---|---|---|---|---|
| **የዝግጅት ምዕራፍ**<br>(የአገራዊ ምክክር አመቻች አካል ማቋቋም፣ የአገራዊ ምክክር ሒደት ቀረፃ፣ ግንዛቤ ማስጨበጥ፣ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎን መወሰን፣ ወዘተ ያጠቃልላል።) | የአገራዊ ምክክር ሒደቱ የሚታመን እና አካታች እንዲሆን አስተዋፅዖ ማድረግ | ▪ ከኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ኮሚሽን ጋር አብሮ መሥራት<br>▪ ስለ አገራዊ ምክክር ግንዛቤ ማጨበጥ (ከሰብዓዊ መብቶች ጋር በተገናኘ መልኩ)<br>▪ የተሳታፊዎች ምርጫ፣ አጀንዳ መምረጥ፣ እና የመሳሰሉ ውሳኔዎችን ለማሳለፍ የሚጠቅሙ የአሠራር ዘዴዎች በሚቀረፁበት ጊዜ መሳተፍ።<br>▪ ሒደቱ ግልጽ እና አካታች በመሆን ታማኝነቱን እንዲያረጋግጥ መሟገት።<br>▪ ለሰብዓዊ መብቶች ርዕሰ ጉዳዮች ቅድሚያ እና ትኩረት መስጠት።<br>▪ ተመሳሳይ ጅምር እንቅስቃሴዎችን ለማስተባበር የሚረዱ መድረኮችን መፍጠር። (ለምሳሌ የሽግግር ፍትሕ) | ▪ የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻዎች እና ሥልጠናዎች<br>▪ አጋርነት<br>▪ ትብብር<br>▪ አድቮኬሲ/ሙግት<br>(ዘመቻዎች፣ አድቮኬሲ እና ሒደቱን የተመለከቱ መረጃዎች መሰብሰብ)<br>▪ ምርመራ ማካሔድ እና ውጤቶችን አሳትሞ ማሰራጨት<br>▪ መድረኮችን መፍጠር | ሕጎች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች ይወጣሉ። እንዲሁም የአጀንዳ አመራረጥ እና አሰባሰብ ሒደቶች አካታች፣ ግልጽ እና አሳታፊ እንዲሆን የሚረዳ የአሠራር ዘዴ ይቀረፃል። |
| **የሒደት ምዕራፍ**<br>(ሒደቱ ላይ መሳተፍ፣ ክትትል እና ትዝብት ማድረግ እና ሒደቱን መመዝገብ እንዲሁም በአጀንዳ መረጣ፣ በምክክሩ ላይ መሳተፍን ያካትታል) | የተመረጡ የሰብዓዊ መብቶች ጉዳዮችን ለአገራዊ ምክክር አጀንዳ እንዲሆኑ ማዘጋጀት | ▪ በአጀንዳ መረጣ እና በምክክር መድረኮች ላይ መሳተፍ<br>▪ በአገራዊ ምክክር መድረክ ላይ መነሳት ያለባቸው የሰብዓዊ መብቶች ጉዳዮችን መምረጥ | ▪ ግንዛቤ ማስጨበጥ<br>▪ አድቮኬሲ<br>▪ አጋርነት<br>▪ ትብብር<br>▪ ክትትል እና ግምገማ | በአገራዊ ምክክር አጀንዳ እና ውጤት ላይ የሚካተቱ የሰብዓዊ መብቶች ርዕሰ ጉዳዮች ይኖራሉ። በተጨማሪም የተገለሉ እና ተጋላጭ የሆኑ የኅብረተሰብ |

| የአገራዊ ምክክር ምእራፍ | የሰብአዊ መብት ድርጅቶች ተሳትፎ ዓላማ | በሰብአዊ መብት ድርጅቶች ሊከናወኑ የሚችሉ ተግባራት | ጠቃሚ ዘዴዎች | ቁልፍ ውጤቶች |
|---|---|---|---|---|
| | | ▪ በአገራዊ ምክክር ሒደት እና ውጤት ላይ መካተት ያለባቸው የተመረጡ የሰብዓዊ መብቶች ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር የአድቮኬሲ ሥራ መሥራት<br>▪ የተገለሉ እና ተጋላጭ ቡድኖችን በምክክር ሒደቱ ተሳታፊ እንዲሆኑ መሚገት<br>▪ ሒደቱ ግልጽነት እንዲኖረው መሚገት | | ክፍሎች በሒደቱ ውስጥ ተካተው ትርጉም ያለው ተሳትፎ ይኖራቸዋል። |
| **የትግበራ ምዕራፍ**<br>(መንግሥት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላትን ጨምሮ ለተለያዩ ባለድርሻ አካላት ከአገራዊ ምክክር በኋላ የተሰጡ ምክረ ሐሳቦችን ወደ ተግባር መቀየር) | ከሰብዓዊ መብቶች ጋር የተያያዙ ምክረ ሐሳቦች መተግበራቸውን ማረጋገጥ | ▪ ከሰብዓዊ መብቶች ርዕሰ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ምክረ ሐሳቦችን ከሚተገብሩ ተቋማት ጋር አብሮ መሥራት<br>የአተገባበሩን ሒደት መከታተል እና መመዝገብ<br>▪ ለብዙኃን እና ለሚመለከታቸው ተቋማት የሰብዓዊ መብቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ምክረ ሐሳቦች በተመለከተ ግንዛቤን የማስጨበጥ ሥራ መሥራት<br>▪ በአገራዊ ምክክር ውጤቶችን አፈፃፀም የሚከታተል አካል እንዲቋቋም መሚገት<br>(የሒደቱን አፈፃፀም ለመከታተል የኮሚሽኑን የቆይታ ጊዜ እንዲራዘም መሚገት ሊሆን ይችላል) | ▪ ግንዛቤ ማስጨበጥ<br>▪ አድቮኬሲ<br>▪ አጋርነት<br>▪ ግምገማ እና ክትትል<br>▪ መመዝገብ | ከሰብዓዊ መብቶች ጋር የተያያዙ ምክረ ሐሳቦች ሙሉ በሙሉ ይተገበራሉ |

## 4.2. በአገራዊ ምክክር ሒደት ከሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶች ጋር የሚሠሩ ባለድርሻ አካላት

የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ዓላማቸውን ለማሳካት ከብዙ ባለድርሻ አካላት ጋር መሥራት ይጠበቅባቸዋል። ወደ አገራዊ ምክክር ሒደት ስንመጣ በሒደቱ ውስጥ ዋና ዋና ባለድርሻ አካላትን መለየት እና በምን መልኩ አብረው መሥራት እንዳለባቸው ማወቅ አስፈላጊ ነው።

**ሰንጠረዥ 2.** የሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶች ጋር የሚሠሩ ባለድርሻ አካላት እና የተሳትፎ ሁኔታ

| ምዕራፍ | ባለድርሻ አካላት | የግንኙነት ሁኔታ |
|---|---|---|
| **የዝግጅት ምዕራፍ** | ▪ የኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ኮሚሽን<br>▪ እንደ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ድርጅቶች ህብረት (ኢሰመድህ) ያሉ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ስብስብ እና በአገራዊ ምክክር ላይ የሚሠሩ ጥምረቶች<br>▪ ለጋሽ አካላት<br>▪ ከአገራዊ ምክክር ጋር በተያያዘ የሚሠሩ ማኅበራት<br>▪ መገናኛ ብዙኃን እና የመገናኛ ብዙኃን ማኅበራት<br>▪ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ግለሰቦች<br>▪ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ)<br>▪ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች እና የሰብዓዊ መብቶች ጉዳይ የሚመለከታቸው አካላት | ▪ ትስስር በመፍጠር በኅብረት መሥራት<br>▪ አጋርነት እና ትብብር |
| **የሒደት ምዕራፍ** | ▪ የኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ኮሚሽን<br>▪ የአገራዊ ምክክር አስተባባሪዎች<br>▪ የአገራዊ ምክክር ተሳታፊ የሰብዓዊ መብቶች ድርጅች እና የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች<br>▪ የአገራዊ ምክክር ተሳታፊ የፖለቲካ ፓርቲዎች<br>▪ መገናኛ ብዙኃን | ▪ አጋርነት<br>▪ አድቮኬሲ<br>▪ ምክክር |
| **የትግበራ ምዕራፍ** | ▪ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን (ኢሰመኮ)<br>▪ ሕግ አውጪ አካላት<br>▪ የፍትሕ አካላት<br>▪ የሚመለከታቸው አስፈፃሚ አካላት | ▪ ትብብር<br>▪ ሙግት<br>▪ ማግባባት |

## 4.3. የሰብአዊ መብቶች ድርጅቶች ሊያጋጥሟቸው የሚችሉ ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ የሚወሰዱ እርምጃዎች

የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ድርጅቶች በአገራዊ ምክክር ሒደት ላይ በሚሳተፉበት ጊዜ የተሳትፎአቸው ውጤት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ብዙ ፈተናዎች ሊያጋጥሟቸው ይችላሉ። የሚከተሉት ዋና ዋና የሚጠበቁ ተግዳሮቶች እና ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ የሚረዱ እርምጃዎች ናቸው።

**ሰንጠረዥ 3.** የሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶች ሊያጋጥሟቸው የሚችሉ ተግዳሮቶች እና የመፍትሔ እርምጃዎች

| ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተግዳሮቶች | ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ የሚወሰዱ እርምጃዎች |
|---|---|
| የሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶችና ተሟጋቾች ደኅንነት | በሰብዓዊ መብት ድርጅቶች መካከል በተለይም በአገራዊ ምክክር በሚሳተፉበት ጊዜ የጋራ ደኅንነት መጠበቂያ ዘዴን መንደፍ |
| በሒደቱ ላይ ግልጽነት ማጣት | ከኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ኮሚሽን እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ቀጣይነት ያለው ግንኙነት መፍጠር |
| በአገራዊ ምክክር ሒደት ዋና ዋና ተግባራት ላይ ለመሳተፍ ዕድል አለማግኘት | ▪ ከኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ኮሚሽን ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ካላቸው ሲቪል ማኅበራት ጋር (የኢትዮጵያ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤትን ጨምሮ) አጋርነት እና ተከታታይነት ያለው የመረጃ ልውውጥ መፍጠር<br>▪ የተሻለ ተፅዕኖ ለማምጣት ከሌሎች ተመሳሳይ ተቋማት ጋር ኅብረት መፍጠር እና ከአገራ ምክክር ኮሚሽን ጋር የመግባቢያ ሥምምነትን ሰነድ መፈረም |
| የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ድርጅቶች ሙግቶችን በሚያደርጉበት ርዕሶች ላይ ልዩ ትኩረት አለመስጠት | የሰብዓዊ መብቶች ጉዳዮች በአገራዊ ምክክር ሒደት ውስጥ እንዲካተቱ ለማድረግ በአግባቡ የታቀደ የዘመቻ እንቅስቃሴ መንደፍ |
| በአገራዊ ምክክር ሒደት ውስጥ ለመሳተፍ የሚያስችል በቂ የሰው ኃይል አለመኖር እና የሀብት እጥረት | ▪ የገንዘብ ማሰባሰብን መንገዶችን ማመቻቸት<br>▪ በሀብት ማሰባሰብ ላይ ከሌሎች ጋር መተባበር ተደጋጋሚ ጥረቶችን ማስወገድ |
| የጊዜ አጠቃቀም | ከአገራዊ ምክክር የጊዜ ሰሌዳ ጋር በተጣጣመ መልኩ የተሳትፎ ፕሮግራሞችን ማቀድ |
| የአገራዊ ምክክር ኮሚሽንን ሚና በጉልህ የሚጫወቱ ተያያዥነት ያላቸው ፕሮጀክቶች መኖር (ለምሳሌ የሽግግር ፍትሕ) | ተያያዥ ሚና ካላቸው ተነሳሽነት ጋር ተመጣጣኝ የሆኑ ዕቅዶችን በመንደፍ ተነሳሽነቱን መደገፍ |

## 4.4. የሥነ ምግባር ደንብ

የሰብአዊ መብቶች ተሟጋች ድርጅቶች በአገራዊ ምክክር ሒደት በሚሳተፉበት ጊዜ በሚከተለው ማዕቀፍ መሠረት መመራት ይኖርባቸዋል። (ሠንጠረዥ 4)

**ሰንጠረዥ 4.** የሰብአዊ መብቶች ተሟጋች ድርጅቶች በአገራዊ ምክክር ሒደት ላይ ሲሳተፉ የሚደረጉ እና የማይደረጉ ነገሮች

| የሚደረጉ | መደረግ የሌለባቸው |
|---|---|
| ▪ አገራዊ ምክክር ከፍተኛ የፖለቲካ ሒደት መሆኑን በመረዳት ጥንቃቄ በተሞላው መልኩ ተሳትፎን ማድረግ<br>▪ አመዛዛኝ እና ምክንያታዊ የሆኑ ድምፆችን ማሰማት<br>▪ በተቻለ መጠን ከብዙ ባለድርሻ አካላት ጋር ግንኙነት መፍጠር<br>▪ በሒደቱ ወቅት ለድርጅታችሁ እና ለአጋሮቻችሁ ለሚሰጠው ግምት መጠንቀቅ<br>▪ ትኩረትን በሰብዓዊ መብቶች ጉዳዮች ላይ ብቻ ማድረግ | ▪ አግላይ እና ከፋፋይ ተግባራት ላይ መሳተፍ<br>▪ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አመፅ ቀስቃሽ ንግግሮችን እና ድርጊቶችን ማበረታታት<br>▪ ወገንተኝነት ከሚያሳዩ አካላት ጋር አጋር መሆን<br>▪ በደንብ የተነደፈ ስትራቴጂ እና የተግባቦት ዕቅድ ሳይኖር ተሳትፎ ማድረግ<br>▪ የተገለሉ እና ተጋላጭ ቡድኖችን ድምፅ ችላ ማለት |

## ማጣቀሻ ሰነዶች


1. Annan, K. (2010). *Kenyan National Dialogue and Reconciliation.*
2. Berghof Foundation. (2017). *National Dialogue Handbook A Guide for Practitioners.* Berline.
3. Berghof Foundation. (2017). *National Dialogue Handbook A Guide for Practitioners: Executive Summary.* Berline: Berghof Foundation.
4. Blunck, M., Vimalarajah, L., Wils, O., Burg, C. v., Lanz, D., & Mubashir, M. (2017). *National Dialogue Handbook: A Guide for Practitioners.* Berline: Berghof Foundation Operations GmbH.
5. Blunck, M., Vimalarajah, L., Wils, O., Burg, C. v., Lanz, D., & Mubashir, M. (2017). *National Dialogue Handbook: A Guide for Practitioners.* Berline: Berghof Foundation Operations GmbH.
6. El-Battahani, A. E.-H. (August 2014). *National Dialogue in Sudan: Past Experiences and Current Challenges.* Khartoum: Sudan Democracy First Group, University of Khartoum. FEP. (2020). *National Dialogue in Ethiopia.* Concept paper.
7. International Crisis Group. (2019). *Keeping Ethiopia's Transition on the Rails. A*frica Report N°283, Brussels.
8. Paffenholz, T., Zachariassen, A., & Helfer, C. (2017). *What Makes or Breaks National Dialogues?* Geneva: Inclusive Peace & Transition Initiative (IPTI) (The Graduate Institute of International and Development Studies).
9. Papagianni, K. (2014). *National Dialogue Processes in Political Transitions.* Brussels, Belgium: Civil Society Dialogue Network.
10. Stigant, S., & Murray, E. (2015). *National Dialogues: A Tool for conflict transformation.* United States Institute of Peace.
11. United states Institute of peace. (2020, 03 07). *National Dialogues: A Tool for*

*Conflict Transformation* - https://www.usip.org/publications/2015/10/national-dialogues- tool-conflict-transformation

12. Yohannes, D., & Dessu, M. K. (2019, March 27). *National dialogues are key to peace in the Horn* - https://issafrica.org: https://issafrica.org/iss-today/national-dialogues-are-key-to-peace- in-the-horn
13. Yohannes, D., & Dessu, M. K. (2019, March 27). *National dialogues are key to peace in the Horn.* - https://issafrica.org: https://issafrica.org/iss-today/national-dialogues- are-key-to-peace-in-the-horn
14. Yohannes, D., & Dessu, M. K. (2020). *National dialogues in the horn of africa: lessons for Ethiopia's political transition.* Addis Ababa: The Institute for Security Studies (ISS).

**አባሪ 1፤** የኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ኮሚሽን አባላት

5. ፕሮፌሰር መስፍን ዓርአያ - ሰብሳቢ
6. ሒሩት ገ/ሥላሴ - ምክትል ሰብሳቢ
7. ዶ/ር ተገኘወርቅ ጌቱ
8. አምባሳደር አይሮሪት መሐመድ
9. ብሌን ገ/መድኅን
10. ዶ/ር ዮናስ አዳዬ
11. ዘገየ አስፋው
12. መለካኩ ወ/ማሪያም
13. አምባሳደር መሐመድ ድሪር
14. ሙልጌታ አጎ
15. ዶ/ር አምባዬ ኦጋቶ

**አባሪ 2፤** የተሳታፊ ድርጅቶች ዝርዝር

## ሀ) በምክክር ዐውደ ጥናት ወቅት ተሳታፊ ድርጅቶች

| ተ.ቁ | የተወከለው ድርጅት ሥም | የመጡበት ክልል |
|---|---|---|
| 1 | የኢትዮጵያ ስርዓተ ፆታ ባለሙያዎች ማኅበር | ባሕርዳር |
| 2 | የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ | ጋምቤላ |
| 3 | የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ | ድሬዳዋ |
| 4 | የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ | ጅግጅጋ |
| 5 | የቤንሻንጉል ጉምዝ ልማት ማኅበራት ኅብረት | ቤንሻንጉል ጉምዝ |
| 6 | አዲስ ህይወት ሪሃበሊቴሽን እንድ ሪኢንተግሬሽን አሶሴሽን | ባሕርዳር |
| 7 | የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ | አዲስ አበባ |
| 8 | የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶች ኅብረት | አዲስ አበባ |
| 9 | የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ማዕከል | አዲስ አበባ |
| 10 | ሰብአዊ መብቶች በኢትዮጵያ ማኅበር | አዲስ አበባ |
| 11 | ኢስት አፍሪካን ኢኒሼቲቭ ፎር ቼንጅ | አዲስ አበባ |
| 12 | ሲቪል ራይት ዲፌንደርስ | አዲስ አበባ |
| 13 | ጉድ ገቨርናንች አፍሪካ (ምሰራቅ አፍሪካ) | አዲስ አበባ |
| 14 | ኸልዝ ኤንድ ሆልነስ ኢትዮጵያ | አዲስ አበባ |
| 15 | የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኛ ሴቶች ብሐራዊ ማኅበር | አዲስ አበባ |
| 16 | ኢትዮጵያን ኢንሼቲቭ ፎር ሂውማን ራይትስ | አዲስ አበባ |

| ተ.ቁ | የተወከለው ድርጅት ሥም | የመጡበት ክልል |
|---|---|---|
| 17 | ሲቪል ሶሳይቲ ሪሶርስ ሴንተር | አዲስ አበባ |
| 18 | ዘላቂ ልማት መካነ ጥናት | አዲስ አበባ |
| 19 | ኢምፓወሪንግ ኔክሰት ጄኔሬሽን | አዲስ አበባ |

## ለ) በማመሳከሪያ ዐውደ ጥናት ወቅት ተሳታፊ ድርጅቶች

| ተ.ቁ | የተወከለው ድርጅት ሥም | የመጡበት ክልል |
|---|---|---|
| 1 | የኢትዮጵያ ስርዓተ ፆታ ባለሙያዎች ማኅበር | ባሕር ዳር |
| 2 | የቤንሻንጉል ጉምዝ ልማት ማኅበራት ኅብረት | ቤኒሻንጉል ጉምዝ |
| 3 | አዲስ ህይወት ሪሃበሊቴሽን አንድ ሪኢንተግሬሽን አሶሴሽን | ባሕር ዳር |
| 4 | ኼር ኢትዮጵያ | ጅግጅጋ |
| 5 | ሴንተር ፎር ፕሮሞቲግ ሂውማ ራይትስ ኤንድ ሰሰተነብል ፒስ ቢውልዲንግ | ጋምቤላ |
| 6 | ሴንተር ፎር ፕሮሞቲንግ ዲሞክራቲክ ካልቸር | ሻሸመኔ |
| 7 | ቸሻየር ኢትዮጵያ | ሃዋሳ |
| 8 | የቤንሻንጉል ጉምዝ ሴቶች ማኅበር | ቤኒሻንጉል ጉምዝ |
| 9 | ዋኪሊሳ ልማት ማኅበር | አፋር |
| 10 | ግሪን ላቭ አፕርሼቲቭ ዴቨሎመንት | ጋምቤላ |
| 11 | ኢምፓወሪንግ ኔክሰት ጄኔሬሽን | አዲስ አበባ |
| 12 | ኼልዝ ኤንድ ሆልነሰ ኢትዮጵያ | አዲስ አበባ |

| ተ.ቁ | የተወከለው ድርጅት ሥም | የመጡበት ክልል |
|---|---|---|
| 13 | የአማራ መልሶ ማቋቋም እና ልማት ማህበር | አዲስ አበባ |
| 14 | ኢትዮጵያን ኢንሼቲቭ ፎር ሂውማን ራይትስ | አዲስ አበባ |
| 15 | የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ማዕከል | አዲስ አበባ |
| 16 | ትራንስፓረንሲ ኢትዮጵያ | አዲስ አበባ |
| 17 | ዘላቂ ልማት መካነ ጥናት | አዲስ አበባ |
| 18 | ሲቪል ራይት ዲፌንደርስ | አዲስ አበባ |
| 19 | የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ካውንስል | አዲስ አበባ |
| 20 | የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኛ ሴቶች ብሔራዊ ማኅበር | አዲስ አበባ |